የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፶፱
አዲስ አበባ ነሐሴ ፪ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 59
ADDIS ABABA 8th August, 2014

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፷/፪ሺ፮ ዓ.ም

ለእንፋሎት ኃይል ዘርፍ ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ......................ገጽ ፯ሺ፬፻፸፯

CONTENTS

Proclamation No. 860/2014

International Development Association Financing Agreement for Financing the Geothermal Sector Development Project Ratification Proclamation..................................Page 7477

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፷/፪ሺ፮

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለእንፋሎት ኃይል ዘርፍ ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፩፻፲፭ ሚሊዮን ፭፻ሺ. ኤስ.ዲ.አር (አንድ መቶ አስራ አምስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ. ኤስ. ዲ. አር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ ጁን ፲ ቀን ፪ሺ.፲፬ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፯ ቀን ፪ሺ.፮ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION No. 860/ 2014

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

WHEREAS, a Financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit in an amount equivalent to SDR 115, 500, 000 (one hundred fifteen million five hundred thousand Special Drawing Rights) for financing the Geothermal Sector Development Project, was signed in Addis Ababa on the 10th day of June, 2014;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Financing Agreement at session held on the 4th day of June, 2014;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለእንፋሎት ኃይል ዘርፍ ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፷/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ ጁን ፲ ቀን ፪ሺ፲፬ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር 5468-ET የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፲፭ ሚሊዮን ፭፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (አንድ መቶ አስራ አምስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ነሐሴ ፪ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for Financing the Geothermal Sector Development Project Ratification Proclamation No. 860/2014".

## 2. Ratification of the Agreement

The Financing Agreement Credit number 5468-ET signed in Addis Ababa on the 10th day of June, 2014 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit an amount of SDR 115, 500, 000 (one hundred fifteen million five hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 8th day of August, 2014.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት